# እራሳችንን ለዓመጽ እናዘጋጅ

(ፍጹም መንገሻ ከኖርዌይ )

የኢትዮጵያ ህዝብ ከግንቦት20 ምን አገኘ? ይልቁንስ ከዚህ ወቅት ጀምሮ ኢትዮጵያ የባህርበር አልባ ሆነች።ክብር ያለው ባንዲራዋ ተለወጠ። አለም የሚያደንቀው የ3000 ዘመን ታሪኳ ውሸት ነው ተባለ።አባቶቻችን ደም እና አጥንታቸውን የገበሩላት መሬቷ ለጎረቤት ሃገሮች ተቆርሶ ተሰጠ።ዓለም የሚቋምጥበት መሬቷ በኢንቬስተር ስም ለባእዳኖች በርካሽ ዋጋ ተቸበቸበ። ከጎረቤት ሃገሮቿ ጋር ያላት ግንኙነት ስጋት ላይ ዋለ። በብሄር  መብት መከበር ስም እና ብሄርን ባማከለው የክልል አደረጃጀት አንድነቷ ስጋት ላይ ዋለ ።ምስኪኑ ገበሬ ተከባብሮ እና ተፋቅሮ ከኖረበት ቀዬው ወደ ክልልህ ተብሎ ተፈናቀለ።ድምጻችን ይከበር ስላሉ ብቻ ውድ ልጆቿ በአጋዚን ጥይት ተገደሉ። የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ለማስከበር ሰራዊቱን የተቀላቀሉ የሰራዊቱ አባላት በመንግስት ተብዬው ለሃገሮች ውለታ መክፈያ ነፍሳቸው ተገበረ። ወጣቱን ትውልድ በወደቀ የትምህት ፖሊሲ ሰባበረው። በኑሮ ውድነት የተነሳ ለአቅመአዳም ያልደረሱ ሴት እህቶቻችን ገላቸውን ሸጠው ለመተዳደር ተገደዱ ከጎዳናም ወጡ።በመልካም አስተዳደር እጦት እና በኑሮ ውድነት ወደተለያየ አለማት የተሰደደው ህዝቧ በተለይም በአረብ ሃገራት ሴቶች ተደፈሩ ሌሎቹም ተገረፉ ተገደሉ። አገሬን ነጻነትን  ፍትህ እኩልነት ያሉ ንጹሃን ዜጎች ደብዛቸው ጠፋ ተገደሉ ከእስር ቤት ታጎሩ ሌላም ሌላም።ይህ መቀጠል አለበትን ????

ያለፉት23 ዓመታት ጭቆና እና ፍትህ ማጣት እንዳይቀጥል፤ እኩልነት እና ዲሞክራሲ በሃገራችን እንዲሰፍን፤ ዘረኝነት እና ጽንፈኝነት ከሃገራችን እንዲጠፉ፤ በሃገራችን እየተካሄደ ያለው የሃገር ማጥፋት እና የዘር ማጥፋት ዘመቻ እንዲቆም፤ መፍትሄው አንድ እና አንድ ነው እሱም ለዚህ ሁሉ ነገር ተጠያቂ የሆነውን የወያኔ ስርዓትን ማስወገድ ብቻ ነው። ይህም ሊሆን የሚችለው

1ኛ የወያኔን ፍጹም የሃገር እና የህዝብ ጠላትነት በሚገባ መረዳት እንደዚሁም ወያኔ መቼም ቢሆን ከጥፋቱ ሊማር እንደማይችል መገንዘብ ማወቅ።

2ኛ ወያኔ ካስቀመጠብን የዘር መርዝ እራሳችንን ማጽዳት በፍጹም ኢትዮጵያዊነት አንድ መሆን።

3ኛ ወያኔን ለማስወገድ የሚደረገው መስዋትነት ለሃገር እና ለትውልድ መሆኑን በመረዳት በሚደረገው ህዝባዊ ዓመጽ አስፈላጊውን መስዋእትነት ለመክፈል እራሳችንን ማዘጋጀት ሙሉ ተሳታፊ መሆን።

4ኛ የተለመዱ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ትብብሮችን መንፈግ።

# ሊደረጉ የሚገባቸው ጥንቃቄዎች

ከታሪክ እንደምንማረው ህዝባዊ እንቅስቃሴ ሲፈነዳ ብዙ ጊዜ ደጋፊዎቹም ተቃዋሚዎቹም ዝግጁ አይደሉም። ይኸም የአሜሪካ እንቅስቃሴ በሞንትጎመሪ ከተማ ድንገት ነበር የጀመረው። ነገር ግን በዚኸን ጊዜ ደጋፊዎቹ እነ ማርቲን ሉተር ኪንግ ዝግጁ ስለነበሩ ድንገት የፈነዳው ህዝባዊ እንቅስቃሴ መረን እንዳይለቅ እየገሩት እና ቀጣይነትም እንዲኖረው እያደረጉ ህብረተሰብን የሚያሻሽሉ ብዙ ተግባሮችን እንዲፈጽም ለማድረግ ችለዋል።ከዚህ የምንማረው አሁን በሃገራችን የሚደረገው ዓመጽ መረን እንዳይለቅ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያስፈልገዋል።

እኛ ኢትዮጵያውያን ወያኔ የተከለብን ተጨማሪ በሽታ ስላለብን ጥንቃቄዓችን የላቀ መሆን ይኖርበታል። ወያኔ በዘር ያደራጀው ጦር ከህዝብ ጋር ይወግናል ብሎ መጠበቅ እጅግ አስቸጋሪ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ወያኔ የተከለብን ዘረኝነት እኛንም ጠልፎ እንዳይጥለን ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል።ለእንደዚህ አይነት ወቅት የሚሆኑ በወያኔ የተደራጁ ዓመጹን የሚያውኩ ጥቂት ግለሰቦች መኖራቸውን በመገንዘብ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ።

ወያኔ በመሃከላችን የተለያዩ ነገሮችን በማንሳት ልዩነትን በመፍጠር ለማደናቀፍ መሞከሩ አይቀሬ ነው እና በአንድነታችን መጽናት።

በዚህ ወቅት ወያኔ በመሃላችን የሚከታቸው በኋላም ከመሃል አፈትልከው የሚወጡ ሆድ አደሮች መኖራቸው በተግባር ያየነው  አይቀሬም ነውና እነሱን ሳይሆን በዓላማቸው ከሚጸኑት ጋር እስከመጨረሻው መጽናት። ሌሎችንም በማስተዋል ለሚደረገው ህዝባዊ ዓመጽ እራሳችንን እናዘጋጅ።ይህ ካልሆነ ጭቆናው እና መከራው ይቀጥላል ሃገር ትጠፋለች።

ወያኔን አንድ ሆነን በማመጽ እናሸመደምደዋለን።

ሕዝብ ያሸንፋል!!!

Kedamawiethiopia@gmail.com